የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ቁጥር አ1162/11/737

ቀን መስከረም 18 ቀን 2015 ዓ.ም.

**ለባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ**

**<u>አዲስ አበባ፣</u>**

ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ነሐሴ 21 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር ባ/ለ/ዲ00552 በተፃፈና የፓርቲው ምክትል ፕሬዚዳንት በሚል በተፈረመ ደብዳቤ የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት ነሐሴ 15 ቀን 2015 ዓ.ም. መደበኛ ስብሰባውን በማካሄድ ያልተሟሉ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን ማሟላቱን እና ነሐሴ 23 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር ባ/ለ/ዲ/00566 በተፃፈ ደብዳቤ የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት መስከረም 29 ቀን 2015 ዓ.ም. ጠቅላላ ጉባኤ እንዲደረግ መወሰኑን አሳውቋል።

ቦርዱ መስከረም 12 ቀን 2015 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ የቀረበውን ሰነድ መርምሯል። በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 14.1 የፓርቲ ብሔራዊ ምክር ቤት እስከ 45 ቋሚ እና 15 ተለዋዋጭ አባላት እንደሚኖሩት፤ በአንቀፅ 14.2 ንዑስ አንቀፅ 2 ብሔራዊ ምክር ቤቱ የጠቅላላ ጉባኤውን መደበኛ፣ ልዩና አስቸኳይ ስብሰባዎች እንደሚጠራ፣ በአንቀፅ 19.7 ንዑስ አንቀፅ 1 በማንኛውም የፓርቲው ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የሆኑ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ እንደተሟላ እንደሚቆጠር፤ በንዑስ አንቀፅ 2 ደግሞ ምልዓተ ጉባኤው ለሁለት ተከታታይ ጊዜ ካልተሟላ ሶስተኛው ተጠርቶ በተገኙት አባላት እንደሚካሄድ ተደንግጓል።

ይሁንና ብሔራዊ ምክር ቤቱ በ15/12/2014 ዓ.ም. ተሰብስቦ የስራ አስፈፃሚ አባላትን ማፅደቁ እና የጠቅላላ ጉባኤ ቀን ወስኗል በሚል በቀረበው ቃለ ጉባኤ 12 አባላት እንደተሰበሰቡ፤ ይህም የሆነው ሁለት ጊዜ ብሔራዊ ምክር ቤቱ ስብሰባ ተጠርቶ ምልዓተ ጉባኤ ባለመሟላቱ ምክንያት እንደሆነ በመግለፅ ስብሰባውን እንደቀጠሉ ተገልጿል። በስብሰባው ላይ ተገኝተዋል ከተባሉት የብሔራዊ ምክር ቤት አባላት መካከል ቦርዱ እውቅና ከተሰጣቸው 45 የብሔራዊ ምክር ቤት አባላት መካከል የተገኙት 7 ብቻ ናቸው።

ለድምጽዎ የሚያምኑን

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚገን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe

ትዊተር
@NEBEthiopia

ኢሜይል
contact@nebe.org.et

ድረ-ገጽ
www.nebe.org.et

ይሁንና የቀረበው ሰነድ ብሔራዊ ምክር ቤቱ በደንቡ አንቀፅ 19.2.2 መሰረት የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በወሰነው ቦታና ጊዜ ሁለት ጊዜ ተጠርቶ እንደነበር እና ምልዓተ ጉባኤውም በሁለቱ የተጠሩ ስብሰባዎች ያልተሟላ የነበረ ስለመሆኑ አያሳይም። በዚሁ መሠረት በ15/12/2014 ዓ.ም. የብሔራዊ ምክር ቤቱ አካሂዶታል የተባለው ስብሰባ ተቀባይነት የሌለው ነው።

በዕለቱ የመጀመሪያው አጀንዳ የነበረው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን ማፅደቅ ሲሆን በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀፅ 16.1 እና 20.1.10 የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ለብሔራዊ ምክር ቤቱ ቀርቦ ከመፅደቁ በፊት በፕሬዚዳንቱ መመረጥ እንዳለባቸው ይደነግጋል። ነገር ግን የፓርቲው ፕሬዚዳንት የመረጧቸው ስራ አስፈፃሚዎች የፀደቁ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማረጋገጫ/ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ብሔራዊ ምክር ቤቱ አሳልፎታል የተባለው ውሳኔ ተቀባይነት አላገኘም።

ሁለተኛው አጀንዳ የጠቅላላ ጉባኤ ቀን መወሰንን በተመለከተ ሲሆን በ12 የብሔራዊ ምክር ቤት አባላት ተደረገ የተባለው ስብሰባ የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ ተከትሎ የተካሄደ ባለመሆኑ በ29/01/2015 ዓ.ም. ጠቅላላ ጉባኤ እንዲደረግ የተላለፈው ውሣኔም ተቀባይነት የሌለው ነው።

ስለሆነም ቦርዱ የፓርቲው ብሔራዊ ምክር ቤት በ15/12/2014 ዓ.ም. ተሰብስቦ አሳልፏቸውን የተባሉትን ውሣኔዎች ያልተቀበላቸው መሆኑን እየገለፅን ፓርቲው በ29/01/2015 ዓ.ም ለማድረግ ያቀደው ጠቅላላ ጉባኤም ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ታዛቢ እንደማይልክ ቦርዱ የወሰነ መሆኑን እናሳውቃለን።

ከበጎ ምኞት ጋር

ብርቱካን ሚደቅሳ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ
ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ